በርካታ የብአዴን አባላት ለእስር ተዳረጉ-ቤተሰቦቻቸውም ወከባና እንግልት ደረሰባቸው፤

ታምራት ላይኔ ለወያኔ ገጸ በረከት የቸረው የወያኔው አማራ ክንፍ ብአዴን ጥቅሙ ተሟጠጠ አባላቱም ከያለበት እየተመነጠሩ ነው

ኮሎኔል አለልኝ የተባለው የአግአዚ ክፍለጦር አስተዳደር የደረሰበት ጠፋ ተባለ፤

ባህር ዳር በእስረኞች መጣበብዋ ተጋለጠ፤

EthioLion.Com

ወያኔ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመቼውም ጊዜ በላይ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት እየወሰደ ባለው ማደናገሪያና ማስመሰያ ስልቱ የተለያዩ ሙያ ያላቸውን ብዙ የሀገሪቱን ዜጎች ለእስር ከመዳረጉም በተጨማሪ ቤተሰቦቻቸው ላይ እንግልትና ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑ ከተለያየ አቅጣጫ የሚደርሰን ዘገባ ገለፀ::

ከሚያዚያ 16 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ወያኔ ግንቦት 7 ተብሎ ከሚጠራው ፓርቲ ጋር ግንኙነት ፈጥረው አደጋ ሊጥሉ ሲሉ ያዝኩዋቸው በማለት የጀመረውን አፈሳ በስፋት ከመቀጠሉም በላይ በታሳሪ ቤተሰቦች እና ዘመዶቻቸው ላይ ከፍተኛ እንግልትና ወከባ እያደረሰባቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን እና የቀድሞው የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር የነበረው የተፈራ ዋልዋን ባለቤት ወ/ሮ ዓይኔ ፅጌን ጨምሮ በርካታ የብአዴን ታጋዮች ለእስር የተዳረጉ ሲሆን በዘመዶቻቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ወከባና እንግልትም እየደረሰባቸው መሆኑን በተለይ ከባህር ዳር የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

አማራ ክልል ብሎ ወያኔ በሰየመው እና በነአያሌው ጎበዜ የሚመራው አስተዳደር ውስጥ ጉዳዩ ስር ሰድዶ ከፍተኛ ትርምስ የፈጠረ ከመሆኑም በላይ የችግሩ ተካፋይ ናቸው የተባሉ የብአዴን ነባር ታጋዮች እና ከፍተኛ ባለስልጣናት እስከ ግልገል ሹማምንቶች ድረስ እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ መሆኑን ከባህር ዳር የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ከወረዳ ካድሬ እስከ ክልሉ ድረስ ያሉት የብአዴን ባለስልጣናት ከያሉበት እየተለቀሙ በባህር ዳር ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ እየታሰሩ ሲሆን ቤተሰቦቻቸውም እንደ ጠላት እየተቆጠሩ በሰደፍ እና በዱላ እየተደበደቡ ከፍተኛ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

መለስ ዜናዊ ለ18 ዓመታት ያለ አንዳች ተቀናቃኝ ስልጣኑን በመያዙ በተለያዩ ስብሰባዎች እና ጉባኤዎች ሲደረጉ የብአዴን ካድሬዎች ጥያቄ ሲያነሱ የነበረና መስዋዕትነት ከፍለን ደርግን ከስልጣኑ የባረርነው የአንድ ሰው አምባገነንነት በመስፈኑ ነው እያሉ ሲያወግዙና ማስተካከያ ይደረግ እያሉ በተደጋጋሚ ጊዜ ቢወተውቱም ከቃላት ሽንገላ ያለፈ አርኪ መልስ ያላገኙት የብአዴን ካድሬዎች ዛሬ ሰበብ ተፈልጎላቸው እንደ ወታደራዊ መኮንኖቹ ሁሉ እነሱም ሰሞኑን ከያሉበት እየታደኑ ወደ ዘብጥያ እየወረዱ መሆኑን ይኸው ከባህር ዳር የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ከደሴ፤ከወልዲያ፤ ከደብረ ብርሀን፤ ከደብረ ማርቆስ፤ ከባህር ዳር ፤ከጎንደር እና ከሌሎችም ከተሞች እየተለቀሙ ባህር ዳር ከተማ በሚገኘው ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ እያጎሩዋቸው መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል ውስጥ ብዙ የክልሉ ባለስልጣናት በምስጢር ለእስር እየተዳረጉ ሲሆን፤ ወታደራዊ መኮንኖች፤ መሀንዲሶች፤ሀኪሞች፤

EthioLion.com

መምህራኖች እና ሌሎችም የህብረተሰቡ ክፍሎች ወደ ዘብጥያ እየወረዱ መሆናቸው ታውቆዋል፡፡

ወታደራዊ ተቋዋሙ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት የምድር ፤የአየር ኃይል መኮንኖች እና ከፌዴራል ፖሊስም በተመሳሳይ ብዙ መኮንኖች በየእለቱ ከሚሰሩበት ቦት ድንገት እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ ከመሆኑም በተጨማሪ የታሳሪዎቹ ቁጥር በመጨመሩ የተነሳ ወደ ተለያዩ እስር ቤቶች እየበታተኑዋቸው መሆኑን ዘገባው ገልፆዋል፡፡

ከአራት ዓመት በፊት ከመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ እንዲሰናበት የተደረገው የብአዴኑ ብ/ጄ/ል አሳምነው ፅጌ ከሚሰራበት የግል ድርጅት ውስጥ ድንገት ትፈለጋለህ ተብሎ ለእስር የተዳረገ ከመሆኑም በተጨማሪ በርካታ በስራ ላይ እና ከስራ ውጭ የሆኑ መኮንኖች እየታሰሩ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ብ/ጄ/ል ከማል ገልቹ የተባለው የኦሮሞ ተወላጅ የክፍለ ጦር አዛዥ አንድ ብርጌድ ጦር ይዞ በመክዳቱ የተነሳ የኦነግ አመለካከት ጦሩ ውስጥ ሰርፆዋል በሚል የኦሮሞ ተወላጅ መኮንኖች ላይ ከፍተኛ እንግልት እና ስቃይ ሲደርስባቸው እንደነበርና በርካቶችም ለእስር ተዳርገው እስከ ዛሬ ድረስ በእስር ላይ እንደሚገኙ የገለፀው ዘገባ አሁን ደግሞ የአማራ ብሄር ተወላጅ መኮንኖችን ሰበብ ፈልጎ በመመንጠር መከላከያን ሙሉ ለሙሉ በህወሀት እጅ እንዲወድቅ ሆን ተብሎ በነመለስ ዜናዊና በበረከት ስምኦን የተሰራ ሂሳብ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

ከእነ ጄ/ል ከማል ገልቹ መክዳት ጋር ተያይዞ ቅርብ ግንኙነት አለህ ተብሎ የኦህዴዱ ሌ/ጄ/ል ባጫ ደበሌ ከምስራቅ እዝ አዛዥነት ወደ መከላከያ የመምሪያ አዛዥነት ዝቅ እንዲልና የአንድ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ እንዲቀመጥ እና ለቁጥጥር እንዲያመች አዲስ አበባ መጥቶ እንዲቀመጥ መደረጉ የሚታወስ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የጦሩ አባላት የአንድ ወገን የበላይነት እየነገሰ መጥቶዋል እንደ ሀገር እናስብ እንጂ እንደ መንደር አናስብ እያሉ ሲወተውት ጦሩን ለአመፅ ልታነሳሱ ነው በሚል በርካታ መኮንኖች እየታፈሱ የታሰሩ ከመሆኑም ሌላ ከስራቸው ላይ ያለምንም ክፍያ የተባረሩ መሆኑንም ዘገባው አስታውሶ ከአንድ ዓመት በፊት የኦሮሞ ተወላጅ መኮንኖችን አሁን ደግሞ የአማራ ተወላጅ መኮንኖችን መንጥረው ካሰሩና ካባረሩ በሁዋላ ሙሉ ለሙሉ የወታደራዊ ተቋዋሙን በህወሀት እጅ እንዲወድቅና እነ መለስ ዜናዊ እንደልባቸው ለማሽከርከር እንዲረዳቸው ያመቻቹት መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

ከመከላከያ ሰራዊት ግምገማ በሚል ሰበብ በጄ/ል ሳሞራ የኑስ ትእዛዝ የተሰናበተው ብ/ጄ/ል አሳምነው በወቅቱ የቅንጅት አመለካከት አለህ ተብሎ እንደነበረ ያስታወሰው ዘገባ የጄ/ሉ ባለቤት ሻለቃ ማዕረግ ያላት የህክምና ባለሙያ የነበራት እና በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ውስጥ ስትሰራ ባለቤቱዋ በተሰናበተ ሰሞን እስዋም

በተመሳሳይ እጣ ከስራ ልትባረር እንደቻለች ዘገባው አስታውሶ አሁንም ጄ/ል አሳምነው ሲታሰር አስዋም ለሰዓታት ታስራ መፈታትዋን ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል፡፡

በ1998 ዓ.ም በነበረው አጠቃላይ ወታደራዊ ግምገማ በጦር ኃይሎች ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት መኮንኖች እርስ በርስ ሲገማገሙ በነበረበት ወቅት የጦር ኃይሎች ዋና አስተዳዳሪ የህወሀትዋ ታጋይ ኮሎኔል እሌኒ የተባለችው የሻለቃ ማዕረግ ያላትን የብ/ጄ/ል አሳምነው ባለቤት አንቺ አቋዋምሽ የቅንጅት ነው በማለት ከስራ ያሰናበተቻት መሆኑን ዘገባው አስታውሶ ይህንን ልትል የቻለችው በ1997 ዓ. ም. በነበረው ግርግር የወያኔ ቅልብ ጦር በጥይት የደበደባቸው ለጋ ህፃናት ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ሲገቡ የህክምና ድጋፍ አድርገሻል በሚል መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

በአልሞ ተኩዋሽ ቅልብ የወያኔ ጦር ተመትተው ጦር ኃይሎች ሆስፒታል የገቡትን ህፃናት እንዲሞቱ ለምን ዝም አላልሽም በሚል ከስራ ያተባረረችው ሻለቃ ሰሞኑን ደግሞ ባለቤትዋ ጄ/ል አሳምነው ሲታሰር አንችም ትፈለጊያለሽ ተብላ ለሰዓታት ታስራ እንደተፈታችና መኖሪያ ቤታቸው በደህንነት ኃይሎች ሲመነቀር እንደነበር ዘገባው ገልፆዋል፡፡

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነው ተፈራ ዋልዋ ባለቤት አይኔ ፅጌ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ከአባትዋ ቤት ውስጥ አፍሶ ለእስር ሲዳርጋት ተፈራ ስብሰባ ላይ እንደነበረና ስብሰባውን ትቶ መጥቶ ለማስፈታት ቢሞክርም ከመለስ የተሰጠ መመሪያ ስለሆነ አንፈታም በመባሉ ወደ መጣበት ሊመለስ እንደቻለ ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

ተፈራ ዋልዋ ያለውን ስልጣን ተጠቅሞ ባለቤቱን ለማስፈታት ቢሞክርም የደህንነት ኃላፊው ጌታቸው አሰፋ ቃሉዋን እስክትሰጥ ድረስ ስለምትፈለግ አንለቃትም በማለት ለተፈራ መልስ ሰጥቶ የሸኘው መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ረቡዕ ዕለት ረፋዱ ላይ ከቀድሞው አውሮፕላን ማረፊያ በታች በኩል ከሚገኘው ገልፍ ክለብ ውስጥ በአንድ ጥቁር መስታወት የተሸፈነ ኮብራ መኪና አራት ሰዎች ወደ ግቢው ገብተው ኮሎኔል ታደሰን የመከላከያ መምሪያ ከፍተኛ ስልጣን ያለውን ሰው ሁለት እጆቹን የሁዋሊት አስረው በጥፊና በእርግጫ እየመቱ ሲወስዱት ማየታቸውን የአይን እማኞች ገልጸዋል፡፡ የአማራ ተወላጅ መኮንኖቹን መታሰር ተከትሎ ብዙ ተራ ወታደሮች ቤተሰቦቻችን ታመዋል በሚል ምክንያት ፍቃድ እንዲሰጣቸው እየጠየቁ ሲሆን ሌሎችም ያለ ፍቃድ ከስራቸው ላይ ጥለው እየጠፉ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ በሰሜን እዝ ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በጄ/ል ሳሞራ የኑስ እና በጄ/ል ሳዓረ መኮንን መሪነት ግምገማ በተጀመረበት ወቅት የጦሩ አባላት ስራቸውን እየተው ወደ ተለያዩ ቦታዎች እየሄዱ ሲሆን ብዙዎቹም

ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ወደ ቤተሰቦቻችን እንድንሄድ ፍቃድ ይሰጠን በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖችን ማስደንገጡ ምንጮቹ ገልፀዋል::

በሰሜን እዝ ውስጥ የጦሩ ግምገማ የተጀመረ ሲሆን ግምገማውን የሚመሩት ጄ/ል ሳሞራ የኑስ እና ሌ/ጄ/ል ሳዓረ መኮንን የሰሜን እዝ አዛዥ መሆናቸው ታውቆዋል:: በዚሁ ግምገማ ላይ በርካታ ጥያዎች የተነሳላቸው እነ ጄ/ል ሳሞራ እንደለመዱት ለማምታታት እና በታሰሩት ጄኔራሎች ላይ ጥፋት ለመለደፍ ቢሞክርም የጦሩ አባላት ግን ያላችሁትን ለመቀበል እንቸገራለን በማለት እያጉረመረሙ መሆኑን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ለ3 ቀናት ይቆያል ተብሎ የተነገረለት የሰሜን እዝ ግምገማ እንደታሰበው ያልተጠናቀቀ ከመሆኑም በተጨማሪ እነ ጄ/ል ሳሞራ በሰራዊቱ ላይ እምነት ስላጡ በመቀሌ የሰማዕታት አዳራሽ ብለው የሚጠሩት መሰብሰቢያ ቦታ ዙሪያ ጥበቃ እንደተመደበና ተሰብሳቢ የጦሩ አባሎች ወደ ስብሰባ አዳራሹ ሲገቡ መሳሪያ እንዳይይዙ እንደተደረገም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በቀጣይም ወደ ተለያዩ የጦሩ ክፍሎች የሚቀጥል ሲሆን በማዕከላዊ እዝ ውስጥ ለማድረግ ታስቦ በሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ የሚመራ በመሆኑ የእነ መለስ ታዛዥ እና ሎሌ ሳሞራ የኑስ በጄ/ሉ ላይ ካለው ጥርጣሬ እና ስጋት የተነሳ ለጊዜው የማእከላዊ እዝ ግምገማ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ያዘዘ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::ወያኔ ወታደራዊ መኮንኖቹን በብሄር ላይ ተመስርቶ ጥቃት መሰንዘር ከጀመረ የቆየ ሲሆን በ1998 ዓ. ም .ያአግአዚ ክፍለ ጦር አስተዳደር ክፍል ኃላፊ የሆነውን ኮሎኔል አለልኝ የተባለውን አስሮ እስከ አሁን ድረስ የት እንዳለ የማይታወቅ መሆኑን ዘገባው አስታውሶዋል::

የአግአዚ ክፍለ ጦር በሲቪል ህብረተሰብ ላይ ጥቃት ሲሰነዝር ሲቆጣና ሲበሳጭ በመታየቱ ፀረ ወያኔ አቋዋም አለው ተብሎ በመጠርጠሩ በእነ መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ኮሎኔል አለልኝ ለስራ ትፈለጋለህ ተብሎ ወደ ቤተ መንግስት ተጠርቶ እንደነበርና እስከ አሁን ድረስ የት እንደደረሰ አለመታወቁን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

በወቅቱ ኮሎኔል አለልኝ በቤተ መንግስት ምድር ቤት ውስጥ መታሰሩን ያስታወሰው ዘገባ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን በህይወት ይኑር ወይም አይኑር በትክክል የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ዘገባው አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በርካታ ሰዎች ከወረዳ ባለስልጣናት እስከ የጦር ጄኔራሎች ድረስ የተጀመረው አፈሳ ቀጥሎ ሰሞኑን

-ጄኔራል አሳምነው

-ኮሎኔል ፋንታሁን ሙሀቤ-በመከላከያ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን የነበረው

-ኮሎኔል ታደሰ-በመከላከያ መምሪያ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበረው

-ሌ/ኮሎኔል ደምሰው -የአማራ ክልል የፀጥታ ከፍተኛ ባለስልጣን

-ሻለቃ አዳሙ ጌትነት፤

-ሻለቃ ሲሳይ፤

-ሻለቃ ባሳዝነው፤

-ሻምበል አዘዘ የተባሉት የታሰሩ ሲሆን ሌሎች ሁለት ጄኔራሎችም በቅርቡ ለእስር ሊዳረጉ ይችላል በሚል የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

እንደ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ አሁን ይፈለጋሉ ከተባሉት ጄኔራሎች መሀከል አንደኛው ሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ ሲሆን ሌላው የአማራ ብሄር ተወላጅ የብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ ያለው ለጊዜው ስሙ ያልተገለፀ እንደሚገኝበትም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት በርካታ መኮንኖች ከያሉበት የጦር ክፍል እየታፈሱ ለእስር በመዳረጋቸው የተነሳ የጦሩ አባላት ቁጣ ሊቀሰቅሱ ይችላሉ ተብሎ ስጋት በመጫሩ ጄኔራሎቹን ማሰር ተጨማሪ ሌላ ቀውስ ሊፈጥር ይችላል በሚል ለጊዜው ሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰና ጄኔራሉን ከማሰር ይልቅ በቅርብ ርቀት ስውር ክትትል እንዲደረግባቸው መወሰኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በቅርቡ በባህ ዳር ከተማ ውስጥ ለሆቴል አገልግሎት የሚውል ህንፃ እያስገነባ ያለው ጄ/ል አበባው ታደሰ ምናልባትም ሙስና በሚል ይህን ሰበብ አድርገው ወደ ዘብጥያ ሊያወርዱት ይችሉ ይሆናል ሲሉ ግምታቸውን ያሰፍራሉ፡፡

በተለይ ከህወሀት ክፍፍል በሁዋላ ብአዴን ትልቅ ድርሻ ይዞዋል እየተባለ ሲያስወሩበት የነበረ ቢሆንም እንደተባለውና እንደተወራበት ብአዴን አንድም የረባ ቦታ ያልያዘ ከመሆኑም በላይ ድርጅቱ የመለስ ታዛዥ እና አጎብዳጅ ሆኖ እስከ ዛሬ የቀጠለ ሲሆን ዛሬ ግን ሙሉ ለሙሉ ባሪያ ሆኖ በመለስ እግር ስር እንዲንበረከክ እነ አዲሱ ለገሰ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸውን ሁኔታውን የተከታተሉ ወገኖች አስረድተዋል፡፡

ሰራዊቱ ውስጥ ወትሮም የህወሀት የበላይነት የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ በህወሀት ጄኔራሎች ስር መውደቁንና ብአዴንም አክርካሪው ተመትቶ እንዲሽመደመድ በበረከት ስምኦን ውስጥ ውስጡን ስራ ሲሰራ ቆይቶ ሙሉ ለሙሉ ስራው መጠናቀቁን የሰሞኑ ድርጊት ገላጭ ነው ሲሉ እነዚሁ ወገኖች አብራርተዋል፡፡

በህወሀት ክፍፍል ወቅት የመለስ ቡድን ከነጉዋዙ ተነቅሎ ሊባረር በተቃረበበት ወቅት መለስ ዜናዊ ብአዴኖችን ድጋፍ እንዲያደርጉለት እነ አዲሱ ለገሰ እግር ላይ ተደፍቶ እንዳልለመነ ዛሬ የብአዴን ነባር ታጋዮችን እያባረረና እያሰረ ድርጅቱ ሙሉ ለሙሉ በመለስ ዜናዊ ስር እንዲንበረከክ የመጨረሻ ስራውን በበረከት ስምኦን አማካኝነት ሰሞኑን ሰርቶ ማጠናቀቁንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በጦሩ ውስጥ የተደራጁት ፀረ ሰላም ኃይሎች የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አድርገው ነበር በሚል ለወያኔ ባለስልጣናት ሲነገር በመደናገጣቸው እና በዓለም አቀፍ

EthioLion.Com

ህብረተሰብ ዘንድ መለስ ከህዝቡ ምን ያህል እንደሚጠላ ማረጋገጫ በመሆኑ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገ ብሎ መግለፁ ተቀይሮ በባለስልጣናት ላይ እና በመንግስታዊ ተቋዋሞች ላይ አደጋ ሊያደርሱ ሲሉ ተያዙ በማለት እንዲሻሻል እና ፕሮፓጋንዳ እንዲሰራ በመለስ ዜናዊ እና በበረከት ስምኦን መወሰኑን ባለፈው ሳምንት መዘገባችን አይዘነጋም::

በመጨረሻም ወያኔ በቅርቡ እያፈሰ ለእስር የዳረጋቸውን ዜጎች ስም ዝርዝራቸውን እና ማንነታቸውን በይገፋ ሊገልፅ ይገባል ሲል እና ድርጊቱን በማውገዝ የአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ድርጅት መግለጫ አወጣ::

የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ድርጅት ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳለው ከሆነ ሰሞኑን 35 ያህል ሰዎች ተያዙ ተብሎ ከተገለፀ በሁዋላ ሌሎችም ብዙዎች መታሰራቸውን አስታውሶ የታሰሩት ሰዎች ማንነት በዝርዝር እና በይፋ ሊገለፅ እንደሚገባና ያሉበት ሁኔታም መገለፅ እንዳለበት አብራርቶዋል::

በአምነስቲ ኢንተርናሽናል መግለጫ የተበሳጨው መለስ ዜናዊ በረከት በሚባለው ፈረሱ በኩል እጅግ ኢትዮጵያዊነትን ባልተላበሰ ሁኔታ ስድብ እና ዝቃጭ ቃሎችን እየተጠቀመ መግለጫ ያወጣ መሆኑም ታውቆዋል:: ከሳምንታት በፊት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቲር በኢትዮጵያ ውስጥ ሰብአዊ ጥሰቶች እንደሚፈጸሙ በዝርዝር በማቅረቡ የተናደዱት እነመለስ ዜናዊ ለአንድ ሳምንት ያህል ጊዜ እስከ ዛሬ የሰሩት ግፍና በደሎችን የሚያጋልጡ ፊልሞችን በማቅረብ ቅስቀሳ ከመስራታቸውም በላይ ሀገር በቀል በሆኑ ድርጅቶች ላይ ማስፈራሪያ መሰንዘራቸው ታውቆዋል::

ሰሞኑን በተከታታይ ለአንድ ሳምንት ያህል የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባወጣው አመታዊ ሪፖርቱ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ ህዝቡ ከፍተኛ በደል እየተፈፀመበት መሆኑን በዝርዝር የገለፀ ሲሆን በአንጻሩ የወያኔ ቡድን ድርጊቱን አስተባብላለሁ በሚል ቀቢፀ ተስፋ ሲፍጨረጨር እስከ ዛሬ የሀገሪቱ ህዝብ ያላወቁት ግፍና እና በደል እየተፈፀመ እንደነበር የሚያሳይና የአሜሪካንን መግለጫ የሚያረጋግጥ ምላሽ መስጠቱ ትዝብት ላይ እንደጣለው ታውቆዋል::

በባሌ እና በኦጋዴን ውስጥ እርስ በርስ ግጭት የተደረገ አስመስለው ያቀረቡት ፊልም በፌዴራል ፖሊስ የተፈጸመውን አረመኔያዊ ተግባር በግልጽና በማያሻማ መልኩ ይፋ አድርገዋል:: ወያኔ በተለይ ኢሰመጉ፤ የቀድሞ መምህራን ማህበር አመራሮች ላይ፤ የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር እና ሌሎችም ድርጅቶችን በሀገር ውስጥ ያለውን ሁኔታ እየተከታተሉ ሪፖርት የሚያደርጉት እነሱ እንደሆኑና ፍርፋሪ ለቃቃሚዎች ናቸው እያለና በቃላት ሊገለጽ የማይችል ስድብ በህዝብ ንብረት በሆነው ቲሌቪዥን በይፋ ሲሳደብ መክረሙም ታውቆዋል::

EthioLion.Com